# ክርስቶስ ብቻ!

ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስ (ከተሰቀለው) ውጪ ሌላ ነገር ላለማወቅ ውሳኔ ያደረገ የወንጌል አገልጋይ ነበር።

"ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር በረቀቀ የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ ልገልጥላችሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና።" (1 ቆሮንቶስ 2:1-2 NASV)

"በክርስቶስ ብቻ" የሚለው ቃል በመቤዠት ውስጥ የክርስቶስ የበላይነት እና የብቃት አዋጅ ነው።

ቤዛነት ለሁሉም የመንፈሳዊ መገለጥ መሠረት ነው። ቤዛነትን መረዳት ማለት ደግሞ የእግዚአብሔርን ልብ ማየት ነው።

"ክርስቶስን ማወቅ" ማለት ጥቅሞቹን ማወቅ ማለት ነው። እንዲሁም በተወለደበት ተፈጥሮ እና ሁኔታ ላይ አለማሰላሰል ማለት ነው። ክርስቶስ ለምን ሥጋ እንደለበሰ እና በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ እስካላወቁ ድረስ ስለ እርሱ ያለውን ታሪክ ብቻ ማወቅ ምን ጥቅም አለው?" ፊሊፕ ሜላንቻቶን

የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ የሚገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ነው። በእግዚአብሔር የተነገረው ቃል፣ በእግዚአብሔር የተሰጠ እምነት፣ በእግዚአብሔር የተዘረጋው ጸጋ፣ ሰው ከሆነው ከእግዚአብሔር ልጅ በቀር ትርጉም ሊሰጥ አይችልም።

የተሐድሶ አራማጁ ማርቲን ሉተር ክርስቶስን ብቻውን የትምህርቱ ማዕከል ያደረገው እና የክርስቶስን ማዕከላዊነት አጽንዖት የሰጠው የክርስቶስን ማንነትና ሥራ በተመለከተ ሐዋርያዊ ምስክርነት ስለተቀበለ ነው።

ክርስቶስ በግል ሕይወታችን እና በቤተክርስቲያን ሕይወታችን ውስጥ ያለውን ማዕከላዊነት እንደገና ማግኘት አለበት። እርሱ ሁልጊዜ የሕይወታችን የትኩረት ነጥብ እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ቀዳሚ መሆን አለበት። ስለዚህ ማንም ወይም ማንም የክርስቶስን ቦታ እንዲወስድ በፍጹም መፍቀድ የለብንም።

በቆሮንቶስ ይገኙ የነበሩ አማኞች ዓይናቸውን ከክርስቶስ ላይ አንስተው በሰዎች ላይ አተኩረው ነበር። በተጨማሪም የግሪክ ፍልስፍና እና የሰው ጥበብ የክርስቶስን ቦታ እንደያዙ እና ዓይኖቻቸውን በእነርሱ ላይ እንዳስቀመጡት እናያለን።

"ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ከቀሎዔ ቤተ ሰብ ሰምቻለሁ፤ ነገሩም እንዲህ ነው፤ ከእናንተ አንዱ፣ “እኔ የጳውሎስ ነኝ” ሲል፣ ሌላው፣ “እኔ የአጵሎስ ነኝ” ይላል፤ ደግሞም አንዱ፣ “እኔ የኬፋ ነኝ” ሲል፣ ሌላው ደግሞ፣ “እኔስ የክርስቶስ ነኝ” ይላል። ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስስ ለእናንተ ተሰቅሏልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠምቃችኋልን? ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በስተቀር ከእናንተ ማንንም ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ስለዚህ በስሜ መጠመቁን የሚናገር ማንም የለም። በርግጥ የእስጢፋኖስንም ቤተ ሰው አጥምቄአለሁ፤ ከእነዚህ ሌላ ግን ማጥመቄ ትዝ አይለኝም። ክርስቶስ የላከኝ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም፤ የክርስቶስም መስቀል ከንቱ እንዳይሆን፣ በሰዎች የንግግር ጥበብ አልሰብክም። የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና፤ “የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤ የዐዋቂዎችንም ዕውቀት ከንቱ አደርጋለሁ።” ጠቢብ የት አለ? ሊቅስ የት አለ? የዘመኑስ ፈላስፋ የት አለ? እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ ሞኝነት አላደረገምን? ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሣ ዓለም በገዛ ጥበቧ እግዚአብሔርን ማወቅ ስለ ተሳናት፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ

የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗል። መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናክል፣ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው። ምክንያቱም ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፤ ከሰውም ብርታት ይልቅ የእግዚአብሔር ድካም ይበረታል።" (1 ቆሮንቶስ 1:11-25 NASV)

ምንም እንኳን ሐዋርያው ጳውሎስ እባቡ በሔዋንን ላይ እንዳደረገው እነዚህ ሐሰተኛ ሐዋርያት አማኞችን በውሸት ትምህርት እንዳያስቷቸው ቢፈራም፣ እጅግ የሚፈራው ግን በአእምሮአቸው ለክርስቶስ ካላቸው ቅንነትና ንጽህና እንዳይስቱ ነው።

"ጥቂቱን ሞኝነቴን እንደምትታገሡኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ በርግጥም እየታገሣችሁኝ ነው። በእግዚአብሔር ቅናት እቀናላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል ዐጭቻችኋለሁና። ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ። ምክንያቱም አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ እኛ ከሰበክንላችሁ ኢየሱስ ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላችሁ፣ ወይም ከተቀበላችሁት መንፈስ የተለየ መንፈስ ብትቀበሉ፣ ወይም ከተቀበላችሁት ወንጌል የተለየ ወንጌል ብትቀበሉ፣ ነገሩን በዝምታ ታልፉታላችሁ ማለት ነው። እኔ ግን “ታላላቅ ሐዋርያት” ከሚባሉት በምንም የማንስ አይመስለኝም። የንግግር ችሎታ ባይኖረኝም እንኳ፣ ዕውቀት ግን አለኝ፤ ይህንም በሁሉ መንገድ በሚገባ ግልጽ አድርገንላችኋል።" (2 ቆሮንቶስ 11:1-6 NASV)

## 1. ክርስቶስ ብቻ አምላክ ነው።

ሀ. ክርስቶስ ከምድራዊ ልደቱ በፊት የዘላለም አምላክ ነው።

🕮 "እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ ሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው። እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ በሁሉ ነገር የበላይነት ይኖረው ዘንድ እርሱ የመጀመሪያ፣ ከሙታን መካከልም በኵር ነው። እግዚአብሔርም ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ ወዶአልና፤" (ቆላስይስ 1:15-19 NASV)

ሌሎች ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ክርስቶስ የማይታየው አምላክ አምሳል መሆኑን ያመለክታሉ።

🕮 "የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል።" (2 ቆሮንቶስ 4:4 NASV)

🕮 "እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራ ቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤ የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።" (ዕብራውያን 1:3 NASV)

"እርሱም የማይታይ አምላክ አምሳል ነው" ይህ ማለት በሰውነታችን አይን አይታይም ማለት ብቻ ሳይሆን እሱ የማይታወቅ ነው ማለት ነው። ይሁን እንጂ በኢየሱስ የማይታወቅ አምላክ የታወቀ ሆነ።

🕮 "እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር። ከአሁን ጀምሮ ግን ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም። ፊልጶስም፣ ጌታ ሆይ፤ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ አንተ ፊልጶስ! ይህን ያህል

ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ፣ አብን አሳየን ትላለህ?" (ዮሐንስ 14:7-9 NASV)

ኢየሱስ ፍጹም የእግዚአብሔር ተወካይና ፍጹም የእግዚአብሔር መገለጫ ነው።

🕮 "ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም፤ ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው።" (ዮሐንስ 1:18 NASV)

🕮 "እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን። እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤ የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።" (ዕብራውያን 1:1-3 NASV)

ክርስቶስ አምላክና የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ በግልፅ ተቀምጧል።

🕮 "እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ። ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጕልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።" (ፊልጵስዩስ 2:6-11 NASV)

🕮 "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ። ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተፈጠረው ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም።" (ዮሐንስ 1:1-3 NASV)

🕮 "ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።" (ኤፌሶን 2:10 NASV)

🕮 "ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤ ክብርና ሞገስ፣ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፤ ሆነዋልምና።”" (ራእይ 4:11 NASV)

ኢየሱስ የፍጥረተ ዓለሙ፣ የመላዕክትና የሰው ፈጣሪ ነው፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው የሚለው መኖርን እንጂ ቀድሞ መፈጠሩን አያሳይም።

ከጳውሎስ በኋላ ከብዙ መቶ ዘመናት በኋላ አሪዮስ የሚባል አደገኛ (ግን ተወዳጅ) መምህር ኢየሱስ ፈጽሞ የባህሪ አምላክ አለመሆኑን እና እርሱ የአብ ፍጥረት እንጂ ከአብ ጋር በመጀመሪያ አልነበረም። ስለዚህ ያልነበረበት ጊዜ አለ ብሎ ተናግሯል። ጳውሎስ ግን ኢየሱስ ከሁሉ ነገር በፊት እንደሆነና እሱ መጀመሪያው እንደሆነ በትክክል ተረድቶ አጥብቆ ተናግሯል።

ቤተክርስቲያን እውነተኛውን አስተምህሮ ለማስጠበቅ ስትል በ325 ዓ.ም በኒቅያ ከተማ አጠቃላይ ጉባኤ በማድረግ ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል የሆነ መለኮታዊ ባህሪ አለው በማለት ወሰነች።

ለ. ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ አምላክ ነው።

🕮 "የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና፤" (ቆላስይስ 2:9 NASV)

ይህ ክፍል የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ ምን ማለት እንደሆነ ጳውሎስ የገለጠበት ነው።

በዚህ ክፍል ክርስቶስ የእግዚአብሔር አምሳል አይደለም። የእግዚአብሔር አምባሳደር ወይም ተወካይም አይደለም። እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ክርስቶስ የመለኮት ፍጹም ሙላት ነው።

የመለኮት ሙላት ምን ማለት ነው? ብርሃን፣ እውነት፣ ኃይል፣ ጥበብ፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ ጽድቅ፣ ቅድስና፣ ህይወት እና ሌሎችም። ስለዚህ ወደ እርሱ ሙላት ምንም ማከል አንችልም።

ክርስቶስ የመለኮት እውነተኛ መገለጥ ሆኖ ይኖራል። ክርስቶስ የመለኮት በሥጋ መገለጥ ነው። ከመጀመሪያው አንስቶ ነበረ፤ ለዘላለምም ይኖራል።

ሐ. ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ አምላክ ነው።

🕮 "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤" (ቆላስይስ 3:1 NASV)

🕮 "አባቶችም የእነርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የትውልድ ሐረጉ የሚቈጠረው ከእነርሱ ነው፤ እርሱም፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ነው፤ አሜን።" (ሮሜ 9:5 NASV)

## 2. ክርስቶስ ብቻ አዳኝ ነው።

🕮 "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፤" (ዮሐንስ 3:16 NASV)

ሀ. በጨለማው አገዛዝ ስር ነበርን።

🕮 "እርሱ ከጨለማ አገዛዝ ታደገን፤ ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን፤" (ቆላስይስ 1:13 NASV)

በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እግዚአብሔር በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለውን ልዩነት አድርጓል። ለምሳሌ በፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር ብርሃንን ቀን እና ጨለማን ሌሊት ብሎ የጠራበትን እናነባለን። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር ብርሃን ተብሎ ተጠርቷል።

🕮 "እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ፤ ብርሃኑን ከጨለማ ለየ። እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ብርሃኑን "ቀን፣ ጨለማውን ሌሊት ብሎ ጠራው። መሸ፤ ነጋም፤ የመጀመሪያ ቀን።" (ዘፍጥረት 1:4-5 NASV)

🕮 "ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምንነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤ የሚል ነው።" (1 ዮሐንስ 1:5 NASV)

እግዚአብሔር ብርሃን ነው። ጨለማም በእርሱ ውስጥ ስለሌለ ጨለማው ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ጋር የሚቃረንን ነገር ማመልከት አለበት። ከእግዚአብሔር ጋር የሚቃረኑ ነገሮች ዓመፅ፣ ኃጢአትና ሞት ይገኙበታል።

- 🕮 "ጨለማና የሞት ጥላ ይውረሱት፤ ደመናም በላዩ ላይ ይረፍ፤ ብርሃኑን ጽልመት ይዋጠው።" (ኢዮብ 3:5 NASV)

- 🕮 "ወደማልመለስበት ስፍራ፣ ወደ ጨለማና ወደ ሞት ጥላ አገር ከመሄዴ በፊት፣ ብርሃኑ እንደ ጨለማ ወደ ሆነበት፣ የሞት ጥላ ወዳረበበበት፣ ሥርዐት የለሽ ወደ ሆነ ምድር፣ ድቅድቅ ጨለማ ወደ ሰፈነበት አገር ሳልሄድ ተወኝ።" (ኢዮብ 10:21-22 NASV)

- 🕮 "በእርግጥ ሰው ማለት እናንተ ናችሁ! ጥበብም ከእናንተ ጋር ትሞታለች! የጨለማን ጥልቅ ነገሮች ይገልጣል፤ የሞትንም ጥላ ወደ ብርሃን ያወጣል።" (ኢዮብ 12:2, 22 NASV)

- 🕮 "ሰው፣ እስከ ጨለማ መጨረሻ ይዘልቃል፤ ከድቅድቅ ጨለማ የማዕድን ድንጋይ ለማግኘት፣ እስከ ውስጠኛው ዋሻ ገብቶ ይፈልጋል።" (ኢዮብ 28:3 NASV)

- 🕮 "ክፉ አድራጊዎች የሚደበቁበት፣ ጨለማ ስፍራ ወይም የሞት ጥላ የለም።" (ኢዮብ 34:22 NASV)

- 🕮 "አንዳንዶቹ በብረት ሰንሰለት ታስረው የተጨነቁ፣ በጨለማ፣ በጥልማሞት ውስጥ የተቀመጡ ነበሩ፤ … ከጨለማና ከጥልማሞት አወጣቸው፤ እስራታቸውንም በጠሰላቸው።" (መዝሙር 107:10፤ 14 NASV)

- 🕮 "በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ ምድር ለኖሩትም ብርሃን ወጣላቸው።" (ኢሳይያስ 9:2 NASV)

- 🕮 "ጨለማን ሳያመጣ፣ በሚጨልሙትም ተራሮች ላይ፣ እግሮቻችሁ ሳይሰናከሉ፣ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ። ብርሃንን ተስፋ ታደርጋላችሁ፤ እርሱ ወደ ጨለማ ይለውጠዋል፤ ድቅድቅ ጨለማም ያደርገዋል።" (ኤርምያስ 13:16 NASV)

- 🕮 "በጨለማ የሚኖር ሕዝብ፣ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ ምድር ላለው፣ ብርሃን ወጣለት።" (ማቴዎስ 4:16 NASV)

- 🕮 "ይኸውም በጨለማ ለሚኖሩት፣ በሞት ጥላ ውስጥም ላሉት እንዲያበራና፣ እግሮቻችንንም ወደ ሰላም መንገድ እንዲመራ ነው።" (ሉቃስ 1:79 NASV)

ከላይ ከተቀመጡት ጥቅሶች በመነሳት በርዕሰ ጉዳዩ ጥቅስ ውስጥ ያለው ጨለማ ኀጢአትንና ሞትን የሚያመለክት ነው ብሎ መደምደም ምንም ችግር የለውም።

ለ. ከእግዚአብሔር የተለየን እና ጠላቶች ነበርን።

- 🕮 "ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች ነበራችሁ።" (ቆላስይስ 1:21 NASV)

ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ላይ ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጠናል።

🕮 "ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም።" (ሮሜ 8:7 NASV)

🕮 "የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!" (ሮሜ  5:10 NASV)

ሐ. መላው ሰውነታችን በኀጢአታዊ ባሕሪ ይገዛ ነበር።

🕮 "በእርሱ ሆናችሁ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ ተገረዛችሁ፤ በክርስቶስም መገረዝ የሥጋን ኀጢአታዊ ባሕርይ አስወገዳችሁ፤" (ቆላስይስ 2:11 NASV)

ጳውሎስ መገረዝ የሚለውን ቃል የሚጠቀምበት ኀጢአተኛውን *ሥጋ* (የኀጢአትን ተፈጥሮ) የማስወገድ (መቁረጥ እና ወርውሮ የመጣል) ዓይነተኛ ምሳሌ በማድረግ ነው።

ሸለፈት ተቆርጦ ሲጣል ምን ይሆናል? ይጠወልጋል፣ ይበሰብሳል፣ ይሞታል እንጂ እንደገና ፈጽሞ አይቀጥልም። በተመሳሳይ ሁኔታ የኀጢአት *ሥጋም* (የኀጢአት ተፈጥሮም) እንደዚያ ነው።

እኛ ኢየሱስን በተቀበልንበት ወቅት አዲስ ፍጥረት በመሆን አዲስ ልብ ተቀብለናል። የኀጢአት *ሥጋችን* (የኀጢአት ተፈጥሮአችን) በመሞቱ የእግዚአብሔርን አዲስ ተፈጥሮ አግኝተናል። ስለዚህ አሁን የኃጢአት *ሥጋ* (የኃጢአት ተፈጥሮ) አይገዛንም።

ክርስቶስ የልባችንን መንፈሳዊ መገረዝ አድርጓል። ስለዚህ አሁን እያየነው ያለው መገረዝ የ*ሥጋ* መገረዝ ሳይሆን የልብ መንፈሳዊ መገረዝ ነው ማለት ነው።

🕮 "አንድ ሰው ለይምሰል በውጫዊው ብቻ ይሁዲ ልሁን ቢል ይሁዲ አይሆንም፤ እውነትኛ ግዝረትም ውጫዊና *ሥጋዊ ሥርዐት* አይደለም። ዳሩ ግን አንድ ሰው ይሁዲ የሚሆነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ ነው። ግዝረትም ግዝረት የሚሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣ በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር ነው። እንዲህ ያለው ሰው ምስጋናው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።" (ሮሜ 2:28-29 NASV)

መ. በኀጢአታችን ውስጥ የሞትን ነበረን።

🕮 "እናንተም በበደላችሁና የ*ሥጋችሁን* ኀጢአታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን ሳላችሁ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፤ ኀጢአታችንንም ሁሉ ይቅር አለን፤" (ቆላስይስ 2:13 NASV)

ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክቱ ላይ ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጠናል።

🕮 "እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤ በዚህም፣ የዓለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ፣ በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ ለሆነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር። እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት የ*ሥጋችንን* ምኞት እያረካን፣ መንገዱንም እየተከተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤ እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣ በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው።" (ኤፌሶን 2:1-5 NASV)

አዲስ ሕይወት ከማግኘታችን በፊት ሞተናል። አንድ ሰው በኢየሱስ ውስጥ ወደ አዲስ ሕይወት ከመምጣቱ በፊት ሐኪም የሚፈልግ የታመመ ሰው ሳይሆን አዳኝ የሚፈልግ የሞተ ሰው ነው።

ሠ. እኛን በሚቃወመን እና በሚጻረረን የዕዳ ጽዕፈት ውስጥ ነበርን።

🕮 "ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ በመደምሰስ፣ በመስቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው።" (ቆላስይስ 2:14 NASV)

ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክቱ ላይ ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጠናል።

🕮 "አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል። ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ራሱ ነውና፤ ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና ከሥርዐቱ ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም ከሁለቱ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ ሰላምን ለማድረግ ነው። ጥልን በገደለበት በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ።" (ኤፌሶን 2:13-16 NASV)

በትዕዛዛት የተፃፈው የዕዳ ፅህፈት እግዚአብሔር በሁለት ጽላቶች ላይ በእጁ ጽፎ በሲና ተራራ የሰጠው ሕግ ሲሆን ዲያቢሎስ ይህን ሕግ ሰዎችን ለመኮነን ይጠቀምበታል።

በጥንቃቄ ስሙ እግዚአብሔር ሕግን ለዲያቢሎስ መሣሪያ እንዲሆነው አልሰጠውም። ነገር ግን ዲያቢሎስ ሕጉ ሰውን እንደሚኮንን ያውቃልና ይህን ዕድል ተጠቅሞ ነው ሰውን የሚኮንንበት። መልካሙ ዜና ግን ይህ ነው ኢየሱስ የመጣው እኛን ለመኮነን ሣይሆን በእኛ ላይ ያለውን ኩነኔ ለመውሰድ ነው። በእርሱ ከሆንን ዳግመኛ ልንኮነን አንችልም።

🕮 "ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም፤" (ሮሜ 8:1 NASV)

🕮 "ስለዚህ አሁን ጉዳይ ተዘግቷል። ከተቀባው ከኢየሱስ ጋር በሕይወት አንድነት በሚቀላቀሉት ላይ ምንም ዓይነት የክስ ድምፅ አይኖርም" (ሮሜ 8፡1 ፓሽን ትርጉም)

ኢየሱስ ሕጉ የሚጠይቀውን ፅድቅ በሙሉ ያሟላ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜ በሚገጥመን ውድቀት ዲያቢሎስ ሕግን ተጠቅሞ ሊኮንነን አይችልም። ምክንያቱም የኢየሱስ መስዋዕት ያለፈውን (past tense) የአሁኑንና (present tense) የወደፊቱን (future) ጊዜ ያማከለ ነውና።

ዲያቢሎስ የትላንት ውድቀታችንን በማሣየት ሕግን ተጠቅሞ ሊኮንነን ሲፈልግ በታላቅ ድምፅ ፅድቅ ስጦታ መሆኑን እንነገረው እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፅድቅ ነኝ እንበለው።

🕮 "በአንድ ሰው መተላለፍ ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሠ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሡ!" (ሮሜ 5:17 NASV)

🕮 "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው።" (2 ቆሮንቶስ 5:21 NASV)

ሰዎች በኩነኔ ውስጥ የሚኖሩት ሕግን ኖሮት በፈፀመውና በመስቀል ላይ በመቸንከር ከመንገድ ባስወገደው በክርስቶስ ኢየሱስ ፍፁም ሥራ ከመደገፍ ይልቅ በራሳቸው አቅም ሕግን ለመፈፀም በመምረጣቸው ነው። በሌላ አነጋገር የኩነኔን አገልግሎት በመምረጣቸው ነው።

🕮 "እንግዲህ እስራኤላውያን ከፊቱ ክብር የተነሣ የሙሴን ፊት ትኵር ብለው ማየት እስኪሳናቸው ድረስ፣ ያ ከጊዜ በኋላ የሚያልፈውና በድንጋይ ላይ በፊደል የተቀረጸው የሞት አገልግሎት በክብር ከመጣ፣ ታዲያ፣ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ከዚያ የላቀ ክብር አይኖረውም? ሰዎችን የሚኰንነው አገልግሎት የከበረ ከሆነ፣ የሚያጸድቀው አገልግሎት የቱን ያህል ይበልጥ የከበረ ይሆን!" (2 ቆሮንቶስ 3:7-9 NASV)

ጳውሎስ አሥርቱን ትዕዛዛት የኩነኔ አገልግሎት ብሎ ይጠራዋል፤ አንዳንዶች ይህን የኩነኔ አገልግሎት የእንሰሳት መስዋዕት ሕግ ነው ይላሉ። ይህ ሕግ ግን በጽላት ላይ ያልተፃፈ ስለሆነ እውነት አይደለም።

ረ. በክፉው ኃይሎች እና ባለሥልጣኖች ስር ነበርን።

🕮 "የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ።" (ቆላስይስ 2:15 NASV)

ክርስቶስ ሰይጣንን፣ ሞትን፣ ሲኦልን፣ ኃጢአትንና መቃብርን ድል አድርጎልናል። ከድል በኋላም ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት በብዙ ምስክሮች መካከል ለ40 ቀናት በህይወት አሳይቷል።

ክርስቶስ ከሞት ሲነሣ አለቆችንና ስልጣናትን ትጥቅ አስፈታቸው። ማለት ስልጣናቸውንና ኀይላቸውን በመግፈፍ (በማጥፋት፣ ሽባ በማድረግ) ምርኮኞች መሆናቸውን በአደባባይ በይፋ እንዲታዩ በማድረግ አደረጋቸው። በሌላ አነጋገር አዋረዳቸው ማለት ነው።

ጆን ማክአርተር ሲገልጽ፡- ሰይጣን መሳሪያውን አጥቷል። ገዢዎች እና ባለ ሥልጣናት (የወደቁ መላእክቶች) በእርሱ [በክርስቶስ] ድል መደረጋቸው በአደባባይ ተገልጠዋል። እዚህ ላይ ያለው ሥዕል እንደ ድል አድራጊው የሮማ ጄኔራል ዓይነት ነው። ድል ያደረጉትን ምርኮኞች በሮማውያን ጎዳናዎች ላይ እንደሚያዝራቸው ነው።

ሰ. ከክርስቶስ ጋር ሕያው አደረገን።

🕮 "እናንተም በበደላችሁና የሥጋችሁን ኀጢአታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን ሳላችሁ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፤ ኀጢአታችንንም ሁሉ ይቅር አለን፤" (ቆላስይስ 2:13 NASV)

ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክቱ ላይ ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጠናል።

🕮 "በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው።" (ኤፌሶን 2:5 NASV)

ሕያው ማድረግ በግሪክ ሲዝፖኤኦ (Syzoopoieo) ሲሆን ከክርስቶስ ጋር እንዲኖር ማድረግ ወይም ከክርስቶስ ጋር ሕይወት መስጠት ማለት ነው።

ሸ. ዳግመኛ ተወለድን።

🕮 "ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር፣ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ከማይጠፋ ዘር ነው።" (1 ጴጥሮስ 1:23 NASV)

🕮 "የፍጥረቱ በኲራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን።" (ያዕቆብ 1፡18 NASV)

### 3. ክርስቶስ ብቻውን በቂ ነው።

ሀ. በክርክር መታለል ማለት እናንተ በእውቀት የበቃችሁ አይደላችሁም ማለት ነው።

🕮 "ማንም ንግግር በማሳመር እንዳያታልላችሁ ይህን እነግራችኋለሁ።" (ቆላስይስ 2:4 NASV)

ጳውሎስ እነዚህ አማኞች በሐሰተኛ አስተማሪዎች ብልህ እና አስደናቂ ንግግር እንዳይታለሉ ግድ አለው።

ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን በሚያባብል ቃል የሚያታልሉ ሰዎች እንዳሉ ያውቃል። ጳውሎስ በኤፌሶን ያሉትን ሽማግሌዎች አስጠንቅቋቸው።

🕮 "እኔ ከሄድሁ በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው በመካከላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና ለመንጋውም እንደማይራሩ ዐውቃለሁ። ከእናንተው መካከል እንኳ የራሳቸውን ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እውነትን የሚያጣምሙ ይነሣሉ። ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትና ቀን ምንም ያህል ሳላቋርጥ በእንባ እያንዳንዳችሁን እንደ መከርኋችሁ አስታውሱ።" (ሐዋርያት ሥራ 20:29-31 NASV)

ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክቱ ላይ ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጠናል።

🕮 "ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም።" (ኤፌሶን 4:14 NASV)

ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚያደርጉት የጌታን ሕዝብ በሚያባብል ቃል "ከክርስቶስ የወንጌል ምስጢር" ውጪ ሌላ ነገር እንዲያምኑ ማሳት ነው።

🕮 "ወንድሞች ሆይ፤ መለያየትን ከሚፈጥሩትና የተማራችሁትን ትምህርት በመቃወም በጕዞአችሁ መሰናክል ከሚያደርጉት እንድትጠነቀቁ አሳስባችኋለሁ፤ ከእነርሱም ራቁ። እንደ እነዚህ ያሉት ሰዎች የሚያገለግሉት ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን፣ የራሳቸውን ሆድ ነው፤ በለሰለሰ አንደ በታቸውና በሽንገላ፣ የዋሆችን ያታልላሉ።" (ሮሜ 16:17-18 NASV)

ለ. በባህላዊ ምርኮኛ ማድረግ ማለት እናንተ ባህላዊ አልሆናችሁም ማለት ነው።

🕮 "በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልማድና በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት ላይ በተመሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ ማግባቢያ ማንም ማርኮ እንዳይወስዳችሁ ተጠንቀቁ።" (ቆላስይስ 2:8 NASV)

በቆላስይስ ሰዎች መካከል ያለው የሐሰት ትምህርት ፍልስፍና እና ባዶ ማታለል ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። የዌብስተር መዝገበ ቃላት ፍልስፍናን ከቴክኒካል መመሪያዎች እና ከተግባራዊ ጥበቦች ውጪ የሚማሩትን ሁሉ ይገልፃል።

በፍልስፍና እና በሰዎች አስተሳሰብ ምክንያት ማንም ሰው ክርስቶስን ከመስማት እንዲያግደን መፍቀድ የለብንም። ደግሞም ማንኛውም ሰው ምንም ያህል ታዋቂ እና ተወዳጅ ቢሆንም በሰዎች ወጎች እንዲያዘን አትፍቀዱለት።

ሁሉም ፍልስፍና ስህተት አይደለም፣ ነገር ግን አታላይ ፍልስፍና ብቻ ነው፤ ውሸት ከውስጥ ተደብቆ ከውጪ ግን ውሸት እውነት መስሎ ይታያል።

በቆላስይስ የሚገኙት ሐሰተኛ አስተማሪዎች ከክርስቶስ እውቀት በላይ የሆነ ምስጢራዊ/ የላቀ እውቀት እንዳላቸው ይናገሩ ነበር። ፍልስፍናው ግን በክርስቶስ እውነት ላይ የተመሠረተ ያልሆነ የሰዎች አስተያየት ነው።

ሁሉም ወጎች የተሳሳቱ አይደሉም፣ ነገር ግን ከክርስቶስ ትምህርቶች ጋር የሚቃረኑ ወጎች ብቻ ናቸው። በሌላ አነጋገር እንደ ክርስቶስ ስብዕና፣ ሥራ እና ትምህርቶች መሠረት አይደሉም።

ሁሉም የሐሰት እና አታላይ ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ እና የሚጻረሩ ወይም እውነቱን ያጣመሙ ናቸው።

በቅዱሳት መጻሕፍት እውነት ውስጥ በደንብ ያልተመሠረቱ ለማታለል እና ውሸቶች የተጋለጡ ናቸው።

የማንኛውም ትምህርት ፈተና ይህ ነው። የክርስቶስን ስብዕናውን፣ መለኮትነቱ፣ በመስቀል ላይ የተጠናቀቀውን ሥራውን፣ ጌትነቱን፣ በሁሉ ላይ የበላይነቱን እና በእርሱ ያለንን ብቁነት ይቀበላል ወይ?

የእግዚአብሔር ቃል እውቀት፣ ማስተዋል እና ጥበብ ከዓለማዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳቦች ይልቅ በጣም ተመራጭ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተቀመጡ መልካም ወጎች ቢኖሩም፣ እነዚህ ግን ከሰዎች ወጎች ጋር መምታታት የለባቸውም።

የሰው ወጎች ከእግዚአብሔር አምልኮና አገልግሎት በፊት ሊቀድሙ አይገባም። በሌላ አነጋገር የሚያስፈልገን ሥርዓት በአምላክ ቃል ውስጥ የተቀመጠ እንጂ የምንኖርበት ክፉ ዓለም የሚያወጣው ሥርዓት ያለው ዝግጅት አይደለም።

ሐ. በሃይማኖት ይፈረድባችኋል ማለት እናንተ ሃይማኖታዊ አይደላችሁም ማለት ነው።

🕮 "እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ በምትጠጡት ወይም በዓልን፣ ወር መባቻንና ሰንበትን በማክበር ነገር ማንም አይፍረድባችሁ፤" (ቆላስይስ 2:16 NASV)

"እንግዲህ" ይህ ቃል ይህንን አስተሳሰብ ከቀደመው አስተሳሰብ ጋር ያገናኛል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ይህን የመሰለ ክቡር ድል ስላሸነፈ በምግብም ሆነ በመጠጥ ወይም በሌሎች ከህጋዊነት ጋር በሚዛመዱ ጉዳዮች ማንም እንዲፈርድባችሁ አንፈቅድም።

የክርስቶስን ባሪያዎች በመምሰል በክርስቶስ ስም መጥተው ነበር። ነገር ግን እነሱ በእርግጥ የሰይጣን መልእክተኞች ናቸው።

ይሁዲዎች በሙሴና በክርስቶስ ተጣምረው ስራውን መጨረስ እንዳለባቸው ያስተምሩ ነበር። ሌሎች ደግሞ ከንቱ ወንጌልን ከእግዚአብሔር መገለጥ ጋር በማደባለቅ ለትክክለኛ መመሪያዎች፣ ለአጉል እምነቶች እና ለሰዎች አመክንዮ በማስተማር ወንጌልን ለማበላሸት ይሻሉ።

በዚህ አዲስ ኪዳን ዘመን በሃይማኖታዊ ስርአታችን በአመጋገብ ልምምዳችን ወይም በቅዱሳን ቀናት ወይም በሰንበት ቀናት መመዘን የለብንም። እነዚህ ነገሮች ብዙውን ጊዜ ከተወሰኑ ቤተ እምነቶች ጋር የተያያዙ ብቻ ናቸውና ከጌታ ቤተ ክርስቲያን ጋር ፈጽሞ መያያዝ የለባቸውም።

መ. ከመንፈሳዊነት ርቃችኋል ማለት በመንፈሳዊ በቂ አይደላችሁም ማለት ነው።

🕮 "ዐጕል ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ የሚወድ ማንም ሰው እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ። እንደዚህ ያለ ሰው ስላየው ራእይ ከመጠን በላይ ራሱን እየካበ በሥጋዊ አእምሮው ከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ ይታበያል፤" (ቆላስይስ 2:18 NASV)

እነዚህ የሐሰት ትሕትና ገጽታዎች እና የመላእክት አምልኮ የቆላስይስ ክርስቲያኖችን ያስጨነቃቸው የሐሰት ትምህርት ክፍሎች ነበሩ።

በቆላስይስ ከነበሩ የሐሰት መምህራን አንዳንዶቹ አንድ ሰው ደኅንነትን እንዲያገኝ ከተፈለገ ለየት የሚል መከራን መቀበልና ራሱን ማዋረድ አለበት በማለት ያስተምሩ ነበር። ከዚህም ጋር አያይዘው መላእክት መመለክ አለባቸው ይላሉ።

በመላአክት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የሰው አስተሳሰብ ነው። ይህ ደግሞ ትኩረታችንን ከኢየሱስ ላይ ለመውሰድ ነው። ደግሞ መልአክት አይመለኩም።

🕮 "እግዚአብሔር፣ አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፤ ወይስ ደግሞ፣ እኔ አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለው ከመላእክት ከቶ ለማን ነው? ደግሞም እግዚአብሔር በኵሩን ወደ ዓለም ሲያስገባ፣ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይስገዱለት ይላል። ስለ መላእክትም ሲናገር፣ መላእክቱን ነፋሳት፣ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደርጋል ይላል። ስለ ልጁ ግን እንዲህ ይላል፤ አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ጽድቅም የመንግሥትህ በትር ይሆናል፤ ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከባልንጀሮችህ በላይ አስቀመጠህ፣ የደስታንም ዘይት ቀባህ። ደግሞም እንዲህ ይላል፤ ጌታ ሆይ፤ አንተ በመጀመሪያ የምድርን መሠረት አኖርህ፤ ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጐናጸፊያ ትጠቀልላቸዋለህ፤ እንደ ልብስም ይለወጣሉ። አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ ዘመንህም ፍጻሜ የለውም። እግዚአብሔር፣ ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ ድረስ፣ በቀኜ ተቀመጥ ያለው ከመላእክት ከቶ ለማን ነው? መላእክት ሁሉ መዳንን የሚወርሱትን ለማገልገል የሚላኩ አገልጋይ መናፍስት አይደሉምን?" (ዕብራውያን 1:5-14 NASV)

ብሉይ ኪዳን ለመላእክት ትልቅ ሥፍራ ስለነበረው ሰዎች ብቁነት እንደሌላቸው በመገንዘብ ከክርስቶስ ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት መላእክትን መካከለኛ አድርገው ይቆጥሩ ነበር። ለክርስቶስ የሚገባውንም ክብር ለእነርሱ ይሰጡ ነበር። ይህ ትህትና መስሎ ቢታይም በእውነቱ ኩራት እና ትዕቢት ነው።

🕮 "እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።" (ቆላስይስ 2:17 NASV)

በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ጥቅሶች ስለ ጥላ ይነግሩናል።

🕮 "እነርሱ ያገለገሉት በሰማይ ላለችው መቅደስ ምሳሌና ጥላ በሆነችው ውስጥ ነው፤ ሙሴ ድንኳኒቱን ለመሥራት በተነሣ ጊዜ፣ በተራራው ላይ በተገለጠልህ ምሳሌ መሠረት ሁሉን ነገር እንድታደርግ ተጠንቀቅ የሚል ትእዛዝ የተሰጠው በዚህ ምክንያት ነበር።" (ዕብራውያን 8:5 NASV)

🕮 "ሕጉ ወደ ፊት ለሚመጡት መልካም ነገሮች ጥላ ነው እንጂ፣ እውነተኛው አካል አይደለም፤ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር ያለ ማቋረጥ የሚቀርበው ተደጋጋሚ መሥዋዕት፣ ለአምልኮ የሚቀርቡትን ሰዎች ፍጹም ሊያደርጋቸው ከቶ አይችልም።" (ዕብራውያን 10:1 NASV)

እነዚያ የብሉይ ኪዳን ጥላዎች ወደ ክርስቶስ ያመለክታሉ። አካሉ (ክርስቶስ) ከጥላው እጅግ የላቀ ነውና የአምልኳችን ዋና አካል እንጂ ጥላ መሆን የለበትም። ዛሬ በብሉይ ኪዳን ጥላ ስር ማምለክ ሳይሆን ክርስቶስን በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ አለብን።

🕮 "እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት እንዲሁ በእርሱ ኑሩ፤ በእርሱ ተተክላችሁና ታንጻችሁ፣ እንደ ተማራችሁት በእምነት ጸንታችሁ፣ የተትረፈረፈ ምስጋና እያቀረባችሁ ኑሩ።" (ቆላስይስ 2:6-7 NASV)

ይህ ለክርስቲያናዊ ኑሮ አስደናቂ ደንብ ነው። በመንፈስ የተጀመረውን በሥጋ ፍጹም ማድረግ አንችልም። ስለዚህ ኢየሱስን እንደተቀበልን ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ በእርሱ መኖር አለብን።

አንድ ተክል መሬት ውስጥ ባለው ሥር አማካኝነት በሚያገኘው ምግብ እንደሚያድግ፣ ልክ እንደዚሁ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም ክርስቶስ ከሰጣቸው ከቃሉ ውስጥ ምግባቸውን በማግኘት ሥር መስደድና መታነጽ አለባቸው። የዘሪው ምሳሌ እዚህ ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

🕮 "በጥሩ መሬት ላይ የተዘራው ዘር ግን ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውለውን ሰው ይመስላል፤ በርግጥም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።" (ማቴዎስ 13:23 NASV)

በእርሱ መመላለስ እና በእርሱ መታነጽ ብቻ ሳይሆን በተማርነው እውነት በመኖር በእምነት መጽናት ብቻ ሳይሆን ምስጋናም የሚበዛልን ልንሆን ይገባናል።

**መጋቢ አለማየሁ ገመቹ**

**ጥቅምት 25/2015 ዓ.ም**